# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ሕንጻ ግንባታን በተመለከተ

## የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ነሐሴ 2004

አዲስ አበባ

# ማውጫ

**ክፍል አንድ** .......... **2**

መግቢያ .......... 2

*የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር* .......... *3*

*የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተግባራት* .......... *4*

*የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር* .......... *5*

*የፋይናንስ ምንጭ* .......... *5*

*ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት* .......... *6*

የኦዲቱ ዓላማ .......... 6

የኦዲቱ ወሰን .......... 6

የኦዲቱ ዘዴ .......... 6

በኦዲት ጭብጡ ዙሪያ ምላሽ ሊያገኙ የሚገባቸው ጥያቄዎች .......... 7

የመመዘኛ መስፈርቶች .......... 7

አሠራር ፍሰት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) .......... 7

*የቅድመ ግንባታ ማመቻቸት ስራዎች* .......... *7*

*የኮንስትራክሽን ክትትልና ቁጥጥር ስራዎች* .......... *8*

*የዕቅድ አፈፃፀምና ግምገማ ስራ* .......... *8*

**ግኝቶች** .......... **9**

የፕሮጀክት ጊዜን እና በጀት በተመለከተ፣ .......... 9

የጨረታ ሂደቶች መዘግየትን በተመለከተ፣ .......... 11

የግንባታ ፕሮጀክቶች ግዥዎችን በተመለከተ፣ .......... 12

የግንባታ እቃዎች አቅርቦትን በተመለከተ፣ .......... 13

**ክፍል ሶስት** .......... **14**

መደምደሚያ .......... 14

**ክፍል አራት** .......... **15**

የማሻሻያ ሀሳቦች .......... 15

**አባሪዎች** .......... **I**

ድርጅታዊ መዋቅር .......... I

የአሰራር ፍሰት ሥዕላዊ መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) .......... II

*የቅድመ ግንባታ ማመቻቸት ስራዎች* .......... *ii*

*የኮንስትራክሽን ክትትልና ቁጥጥር ስራ ሥዕላዊ መግለጫ* .......... *iii*

*የዕቅድ አፈፃፀምና ግምገማ ስራ ፍሰት ሥዕላዊ መግለጫ* .......... *iv*

የኦዲት ጥያቄዎች .......... V

የመመዘኛ መስፈርቶች .......... VI

ዋና ዋና የባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት .......... VII

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ቀደም ሲል የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በ1998 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 471/98 ተቋቁሞ የመንግሥት የልማት አቅጣጫን በመከተል የከተማን፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን እና የመንገድ ዘርፍን እንዲመራና እንዲያስተባብር ኃላፊነት ተሰጥቶታል። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 ስያሜው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚል በአዲስ መልክ የተደራጀ ሲሆን፣ ይህ ሚኒስቴር መ/ቤት እንዲያስፈጽም ከተሰጡት ተግባራት መካካል አንዱ በፌዴራል መንግስት በጀት የሚሰሩ ሕንጻዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ ማድረግ ነው።

2. አስፈጻሚ አካላት በመንግስት የሚታቀዱትን የልማት መርሐ ግብሮች ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችላቸው የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ምቹ የስራ አካባቢ እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመንግስት ቢሮ ሕንጻዎች ግንባታ ጥያቄ እየተበራከተ መጥቷል። ይህንንም ሁኔታ መንግስት ቀደም ብሎ በመገንዘቡ ምክንያት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በጥራት የተሰሩ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ እና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ቢሮዎችን በባለቤትነት እያስገነባ ለመ/ቤቶች እንዲያስረክብ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ካለው የስራ ስፋትና ከሚፈለገው የጥራት ደረጃ አንጻር ስራውን በመደበኛነት የሚከታተል እና የሚሰጠውን አቅጣጫ ተቀብሎ ግንባታውን የሚያስፈጽም የፕሮጀክት ጽ/ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከሰኔ አንድ ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ተቋቁሞ ስራውን እያከናወነ ይገኛል።

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

4. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል:-

- ✓ በፌዴራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎቹን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፤
- ✓ የከተሞች አከታተምን በሚመለከት ጥናት ማካሄድ፣ ለከተሞች ደረጃ መመዘኛ ማውጣት፤
- ✓ ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ መስጠት፤ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ የአቅም ግንባታ እገዛ ማድረግ፤
- ✓ ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናት ማድረግ፣ ተግባራዊ እንዲሆን ማገዝና አፈጻጸሙን መከታተል፤
- ✓ ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ የከተማ አስተዳደሮችን የሥራ እንቅስቃሴዎች መከታተል፤
- ✓ የከተማ ነዋሪው ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ የመኖሪያ ቤት እንዲሠራ አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ለተግባራዊነታቸውም ለከተሞች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ፤
- ✓ ለሌሎች አካላት በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ለኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች ማውጣትና መከበራቸውን መከታተል፤ ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ማድረግ፤
- ✓ መሐንዲሶችንና አርክቴክቶችን መመዝገብ፣ የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፣ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ መወሰን፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት ለሚችሉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፤

- ✓ በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ማካሄድ፤
- ✓ በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶች አስተዳደር በአግባቡ እንዲከናወን መደረጉን ማረጋገጥ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተግባራት

5. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንጻዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

- የቢሮ ሕንጻ እንዲገነባላቸው ለተፈቀደላቸው የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በቂና አመች የህንጻ መገንቢያ ቦታ እንዲኖርና ቦታው ከልዩ ልዩ ንብረቶች ነጻ እንዲሆን በማድረግ ለግንባታ ያዘጋጃል፣
- ለግንባታ ቦታ የተመረጡ ቦታዎች የአፈር ምርመራ በማሰራት ውጤቱን ከአስተያየት ጋር ለቢሮ ኃላፊው ያቀርባል፣
- ለግንባታው አግባብ ካለው የመንግስት አካል የግንባታ ፈቃድ ያወጣል፣
- የተቋራጮች መረጣ እና የሎጀስቲክስ አቅርቦትን በሚመለከት በጥናት ላይ የተመሰረተ ለዕቅድ ዝግጅት የሚሆን ሃሣብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል፣
- ለፕሮጀክት ግንባታና ሳይቶች የግብዓት ምርቶች ማምረቻ ቦታዎች ላይ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ በመመደብ፤ ከአጠቃላይ የፕሮጀክቶቹ መርሃ ግብር አንጻር በማገናዘብ በተቋራጮቹ የሚቀርቡ ዝርዝር መርሃ ግብሮችን መርምሮ በማጽደቅ እና ለክፍያዎች ማረጋገጫ በመስጠት በአጠቃላይ በፕሮጀክቱ ክንውን ላይ ክትትል በማድረግ በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤
- የፕሮጀክት አፈጻጸም ዝርዝር የስራ ዕቅድ እና የፕሮጀክት መሃንዲሶች የሚሰሩበትን የስራ መመሪያ ያዘጋጃል፣

- ስለግንባታው ስራ አካሄድ በጽሁፍ፣በፎቶ ግራፍና በፊልም የተደገፈ መረጃ ይይዛል፣
- ለፕሮጅክቱ የሚያስፈልገውን የሰው ሃብት የማቴሪያልና የገንዘብ አጠቃቀም እቅድ ያዘጋጃል ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል፣
- ስለፕሮጀክቱ አፈጻጸም፣ስለአጋጠመው ችግርና ለችግሩ ስለተሰጠው መፍትሄ ሳምንታዊ፣ወርሃዊ፣የሩብ ዓመትና ዓመታዊ ሪፖርት ለመኖሪያ ቤቶችና የመንግስት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ ያቀርባል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር

6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሆኖ በአንድ ሚኒስትርና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ይመራል፡፡ ለሚኒስቴሩ ተጠሪ የሆኑ አንድ የኦዲት መምሪያና አሥራ አንድ ቢሮዎች ያሉት ሲሆን፣ እነርሱም የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ፣ የፖሊሲና ኘሮግራም ቢሮ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ፣ የከተማ ኘላን ጽዳትና ውበት ቢሮ፣ የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንፃዎች ግንባታ ቢሮ፣ የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ፣ የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ (በሥሩ ፋይናንስን ይይዛል) እና የኢንተርኘራይዞች ልማትና የመንግሥት ቤቶች አስተዳደር፣ ክትትልና ድጋፍ ቢሮ ናቸው፡፡ የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንፃዎች ግንባታ ቢሮ ስር የፌዴራል መ/ቤቶችን ቢሮ የሚያስገነባው የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚገኝ ሲሆን ይህ ጽ/ቤት አንድ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ፣ ሁለት የመስክ መሐንዲሶች እና አንድ ጸሐፊ እንዲኖረው ተደርጎ ተደራጅቷል (አባሪ 1) ፡፡

## የፋይናስ ምንጭ

7. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የገቢ ምንጭ ከመንግስት የሚመደብ በጀት ሲሆን፣ በ2001፣ በ2002፣ እና በ2003 በጀት ዓመት ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተመደበ በጀት ብር 51.3 ፣ 86.3፣ እና 195.0 ሚሊየን በቅደም ተከተል ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በ2001 ብር 55.1፣ በ2002 ብር 86.5 እና በ2003 በጀት ዓመት ብር 66.1 ሚሊየን ወጪ ተደርጓል፡፡

## ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት

8. ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተጨማሪ በግንባታው ሂደት ሌሎች ዋና ዋና ተዋናዮች አማካሪዎች፣ ህንፃ ተቋራጮች እና የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሲሆኑ እነዚህ አካላት በፕሮጀክቱ ክንውን ላይ ወሳኝ ድርሻ አላቸው ( አባሪ 5)፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

9. የኦዲቱ አላማ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚካሄዱ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ቢሮ ሕንጻ ግንባታዎች በኢኮኖሚ፣ በብቃትና በቅልጥፍና እየተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ አፈጻጸሙ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ አጥጋቢ እንዳይሆን ያደረጉትን ችግሮች በመለየት እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚያግዙ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለስራ አመራሩ ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰን

10. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከተገነቡ እና እየተገነቡ ካሉት አስራ አምስት ፕሮጀክቶች ውስጥ በኦዲቱ የተካተቱት በናሙና የተለዩት ስምንት ፕሮጀክቶች ሲሆኑ፣ ሦስት ግንባታቸው የተጠናቀቀ ፕሮጀክቶች (ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን)፤ አምስት በግንባታ ሂደት ላይ ካሉት ውስጥ (ፕሬስ ድርጅት፣ማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ፣የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ፍትህ ሚኒስቴር እና የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ተጨማሪ አንድ ብሎክ) ሕንጻ ግንባታ ናቸው፡፡ሁሉም የግንባታ ፕሮጀክቶች በአዲስ አበባ የሚገኙ ሲሆን፣ በኦዲቱ የሸፈነው ከ2001-2004 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ የተከናወኑ ስራዎችን ነው፡፡

## የኦዲቱ ዘዴ

11. ኦዲቱ የተከናወነው በዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች ድርጅት የኦዲት ስታንዳርድ እና በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች መሠረት ሲሆን፣ የኦዲት ሥራው የሚረዱ ማስረጃዎች የተሰበሰቡት የጽሁፍ መረጃዎችን በመከለስ፣ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ በግንባታ ፕሮጀክት ሳይቶች

በአካል በመገኘት ምልከታ ማድረግ እና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተንና በማጠናቀር ነው፡፡

## በኦዲት ጭብጡ ዙሪያ ምላሽ ሊያገኙ የሚገባቸው ጥያቄዎች

12. በኦዲት ጭብጡ ዙሪያ ምላሽ ሊያገኙ የሚገባቸው አምስት ጥያቄዎች በኦዲት ቡድኑ ተቀምጠዋል፡፡ዝርዝሩ በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

## የመመዘኛ መስፈርቶች

13. በኦዲት ቡድኑ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ ሰባት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል (አባሪ 4 )፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም የኦዲት ተደራጊዎች አስተያታቸውን እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸዋል፡፡

## አሠራር ፍሰት መግለጫ (Process Description)

14. አዲስ ሕንፃ እንዲገነባላቸው የሚፈልጉ የፌዴራል መንግስት (ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ኤጀንሲዎች ወይም ባስልጣን) መስሪያ ቤቶች ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥያቄያቸውን በደብዳቤ ያቀርባሉ፣ ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደብዳቤ ይጽፋል፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የህንፃ ግንባታ ውሳኔውን እና በጀቱን ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ያሳውቃል፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የታቀዱትን የቢሮ ህንጻ ግንባታዎች ከቅድመ ግንባታ ማመቻቸት እስከ ማጠናቀቅ እና ማስረከብ ድረስ ያለውን ስራ ይሰራል፡፡ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ህንፃ ግንባታ የሚጠቀመው ተመሳሳይ (standard) እና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ዲዛይኖችን ነው፡፡

### የቅድመ ግንባታ ማመቻቸት ስራዎች

15. ከአስፈፃሚ አካላት በሚቀርቡ የቢሮዎች ግንባት ፍላጎት መሰረት ግንባታው የሚያርፍበትን ቦታ መምረጥና ከሚመለከተው አካል ፍቃድ የማግኘት፣ የአፈር ምርመራ፣ የዲዛይን አዳፕቴሽን ስራ፣ የግንባታ ፍቃድ ማግኘት፣ እንዲሁም ስራውን ሊሰራ የሚችል የተቋራጭ መረጣና የሎጀስቲክ አቅርቦት ዝግጅትና ማመቻቸት ስራዎች የሚከናወንበት የስራ ሂደት ነው፡፡የፕሮጀክት ተቋራጮች

(ዋናው ተቋራጭ፣ ንዑስ ተቋራጮች እና አማካሪዎች) የሚመረጡት በግልፅ ጨረታ ስርዓት ሲሆን የጨረታው ሂደት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ እና በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ትብብር የግምገማ እና አሸናፊውን የመለየት ስራ ይሰራል፡፡ የጨረታ አሸናፊው ድርጅት አሸናፊነቱ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ቀርቦ ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር ውል ይፈራረማል፡፡

## የኮንስትራክሽን ክትትልና ቁጥጥር ስራዎች

16. የኮንስትራክሽን ክትትልና ቁጥጥር ስራ ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ መርሃ ግብሮችን መመርመርና ማፅደቅ፣ ግንባታዎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ጥራታቸውን ጠብቀው መሰራታቸውን መከታተል፣ ክፍያዎችን በማረጋገጥ የማስተላለፍ እንዲሁም መረጃዎችን የመሰብሰብና የማጠናቀር ስራዎች የሚከናወኑበት የሥራ ሂደት ነው::

## የዕቅድ አፈፃፀምና ግምገማ ስራ

17. የዕቅድ አፈፃፀምና ግምገማ ስራ ለስራ ሂደቱ የሚያስፈልገውን አጠቃላይ ዕቅድ በማዘጋጀት እንዲሁም የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም በመገምገም እና ወቅታዊ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል የሚቀርብበት የስራ ሂደት ነው፡፡

18. የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚያስገነባቸው ቢሮዎች በግል የሕንፃ ተቋራጮች ሲሆን፣ ጽ/ቤቱ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብዓቶችን (ሲሚንቶ፣ ብረት፣ ፕሪካስት ቢም እና ስላብ ብሎኬቶች) የሚያቀርብ ሲሆን፣ የአማካሪ መሀንዲሶችን በመቅጠር እና በራሱ ባለሙያዎች የቁጥጥር ስራውን ያከናውናል፡፡ የአሰራር ፍሰት ስዕላዊ መግለጫ በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡


# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## የፕሮጀክት ጊዜን እና በጀት በተመለከተ፣

19. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስር የሚከናወኑ የቢሮ ሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እና የገንዘብ በጀት ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡

20. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እያከናወናቸው ያሉ እና የተጠናቀቁ የቢሮ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ያሉት እና የተከናወኑት ከተያዘላቸው የጊዜ በጀት በላይ በመውሰድ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡




ስዕል 1.ግንባታቸው የዘገየ ፕሮጀክቶች

(*ምንጭ: የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፋይሎች*)

21. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው በስምንት ወር ውስጥ እንዲጠናቀቁ ታስበው የተጀመሩ ሦስት ፕሮጀክቶች እያንዳንዳቸው ከታቀደላቸው ግዜ በላይ ሁለት ዓመታት በመውሰድ የተጠናቀቁ ሲሆን፣ ይሄም በመቶኛ ሲሰላ እነዚህ ፕሮጀክቶች ከእቅዳቸው በላይ 300% እንደወሰዱ ያሳያል፡፡ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኦዲቱ ወቅት ከታዩ እና በመጠናቀቅ ሂደት ላይ ካሉ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንደኛው ሲሆን ፕሮጀክቱን ለመገንባት የዘጠኝ ወር እቅድ ተይዞ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ ከሶስት አመት በላይ መውሰዱ ተረጋግጧል፡፡

22. በኦዲቱ ወቅት ከታዩ አምስት በግንባታ ላይ ካሉ ፕሮጀክቶች ውስጥ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስተር ተጨማሪ ብሎክ ህንፃ ግንባታ በጥቅምት 2001 የተጀመረ ሲሆን፣ የዚህ ፕሮጀክት የግንባታ መጠናቀቂያ ጊዜ ሐምሌ 2001 እንዲሆን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም እስከ ሰኔ 2004 ድረስ ፕሮጀክቱ እንዳልተጠናቀቀ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የፍትህ ሚኒስቴር የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት በሐምሌ 2001 እንዲጠናቀቅ ታስቦ ህዳር 2001 ላይ ተጀምሯል ሆኖም ግን እስከ ሰኔ 2004 ድረስ የተከናወነው የህንፃ ግንባታው 58% ብቻ እንደሆነ ታውቋል፡፡

23. በሚኒስተር መ/ቤቱ እና በኮንትራክተሮች መካከል በተፈረመው የኮንትራክት ስምምነት መሰረት የግንባታ እቃዎች የሚቀርቡት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ ከቀረበላቸው የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ምላሽ እንዲሁም በተለያየ ጊዜ ከስራ ተቋራጮች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከተጻፉ ደብዳቤዎች የግንባታ እቃዎች በወቅቱ አለመቅረብ የኮንስትራክሽን ግንባታዎች በተደጋጋሚ ለወራት እንዲቆሙ ምክንያት እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

24. በዚህ ዙሪያ የመ/ቤቱ ሀላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ለፕሮጀክቶቹ መዘግየት ምክንያቶች በግንባታ እቃዎች አቅርቦት/ስርጭት ላይ ያሉ ችግሮች እና የስራ ተቋራጮች አቅም ውሱንነት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

25. የቢሮ ህንጻ ግንባታዎች መዘግየት ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው የገንዘብ በጀት በላይ እንዲያስወጡ የሚያደርግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቢሮ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው የገንዘብ በጀት በላይ 8.7 ሚሊዮን ብር ያስወጡ ሲሆን፣ ይህም በአማካይ ሲሰላ የየፕሮጀክቶቹን ወጪ በጀት 20% ይጠጋል፡፡

**ሰንጠረዥ 1.**<u>የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የዋጋ ማስተካከያ በሚሊየን ብር</u>

| የፕሮጀክቱ ስም | የቀድሞ ኮንትራት ዋጋ | የተሻሻለው ኮንትራት ዋጋ | ልዩነት | ልዩነት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| የግብርና ሚኒስቴር | 13.8 | 17.2 | 3.4 | 24.6% |
| የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | 14.7 | 17.5 | 2.7 | 18.0% |
| የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን | 14.7 | 17.2 | 2.5 | 17.0% |
| **በድምሩ** | **43.2** | **51.9** | **8.7** | **20.6%** |

(ምንጭ፡ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፋይሎች)

27. ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው የጊዜና የወጪ በጀት በላይ እንዲወስዱ በፕሮጀክቶቹ የስራ ዝርዝር (bill of quantities) እና ፕሮጀክቶቹ ግንባታ ላይ በተግባር በሚጠቀሙት የግብዓቶች መጠን መካከል ያለው ሰፊ ልዩነት እንደ አንድ ምክንያት ተቀምጧል፡፡ በኦዲቱ

ወቅት እንደታየው ለስታስቲስቲክስ ኤጀንሲ የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ከመሬት በታች የሚከናወን ግንባታ ሥራ (substructure work) ለማካሄድ በስራ ዝርዝር (bill of quantities) እና ፕሮጀክቱ በተጠቀመው ግብአት መካከል ያለው ልዩነት ወደ ግማሽ ሚሊዮን ብር እንደሚጠጋ ታውቋል፡፡

28. ለፕሬስ ድርጅት የቢሮ ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት በስራ ዝርዝር (bill of quantities) እና ፕሮጀክት ዲዛይን አለመጣጣም ምክንያት ተጨማሪ 22,434 ኪሎ ግራም ብረት አስፈልጎ የነበረ ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው በተደጋጋሚ ያጋጠሙ ተመሳሳይ ልዩነቶች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱን የተሻሻለ የስራ ዝርዝር(bill of quantities) ከአማካሪው እንዲጠይቅ እንዳስገደደው ታውቋል፡፡

## የጨረታ ሂደቶች መዘግየትን በተመለከተ፣

29. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚካሄዱ ግዥዎች በመንግስት የግዥ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡

30. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከጨረታ በኋላ አሸናፊውን ለማሳወቅ እና ኮንትራት ለመፈራረም የሚወስደው ጊዜ በግዥ መመሪያ ላይ ከተቀመጠው በላይ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 16 መሰረት የጨረታ አሸናፊዎችን ለመግለፅ እና ኮንትራት ለመፈራረም የተቀመጠው ጊዜ ጨረታው ከተከፈተ በኋላ 60 ቀን ያህል ሲሆን፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በግንቦት 2002 ለማእከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ፣ ለፕሬስ ድርጅት እና ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ተጨማሪ ብሎክ ለማሰራት ጨረታ ካወጣ በኋላ ኮንትራት ለመፈራረም 9 ወራት ያህል ወስዶበታል፡፡

31. ይህን በተመለከተ የመ/ቤቱ ሀላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የጨረታ መዘግየቱ ሊከሰት የቻለው በወቅቱ የስራ ሂደት አደረጃጀት ለውጥ በመደረጉ፣ የሳይቶች ዝግጅት በመዘግየቱ እና ለግንባታ የተመረጠ ቦታ ባልተዘጋጀበት ጨረታውን ማስቀጠል ባለመቻሉ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

32. በጨረታ ሂደቶች ላይ የሚታዩ መዘግየቶች ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው የጊዜና የወጪ በጀት መሰረት እንዳይከናወኑ የሚያደርግ ሲሆን፣ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶች ላይ የሚፈጠሩ መዘግየቶች ህንፃ እንዲገነባላቸው እየተጠባበቁ ላሉ መ/ቤቶች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ምቹ የስራ አካባቢ እንዳይኖራቸው እና በወቅቱ እንዳይስተናገዱ ያደርጋል፡፡

## የግንባታ ፕሮጀክቶች ግዥዎችን በተመለከተ፣

33. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚካሄዱ ግዥዎች በመንግስት የግዢ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡

34. በመንግስት የግዥ አዋጅ እና መመሪያ ላይ የተቀመጡ ስድስት አይነት የግዥ ዘዴዎች ያሉ ሲሆን ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ከነዚህ ዘዴዎች ውጪ ግዥ ለመፈፀም ቢፈልግ ከመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ምክንያቱን በመግለፅ ፍቃድ ማግኘት እንዳለበት ተገልጿል፡፡

35. በኦዲቱ ወቅት የታዩት ስምንት ፕሮጀክቶች በሙሉ በግዥ አዋጅ ላይ ከተቀመጡት የግዥ ዘዴዎች ውጪ የተሰጡ ቢሆንም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለአምስት ፕሮጀክቶች ትክክለኛ ምክንያት በማቅረብ ከመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የይሁንታ ፍቃድ አግኝቷል፡፡

36. ሆኖም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አንዳንድ የግንባታ ፕሮጀክቶችን ለኮንትራክተሮች ሲሰጥ የመንግስት የግዥ አዋጅ እና መመሪያን ሳይከተል እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 8 ፕሮጀክቶች ውስጥ ሶስቱ ካለጨረታ በቀጥታ ለአንድ ሕንጻ ስራ ተቋራጭ ተሰጥተው ተገኝተዋል፡፡ ፕሮጀከት ጽ/ቤቱ ሶስቱን ፕሮጀክቶች ለአንድ ስራ ተቋራጭ (ለተገጣጣሚ ሕንጻ አካላት ማምረቻ ድርጅት) በቀጥታ ለመስጠት ከመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ፍቃድ ሲጠይቅ የድርጅቱን ውጤታማነትን እና ብቃትን እንደ ምክንያት አቅርቦ ነበር፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት እንደተረጋገጠው ግን ለሚኒስተር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆነው የተገጣጣሚ ሕንጻ አካላት ማምረቻ ድርጅት ፍቃድ በተጠየቀበት ወቅት በእዳ ውስጥ ሆኖ ኪሳራ ላይ ይገኝ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

37. ለተገጣጣሚ ሕንጻ አካላት ማምረቻ ድርጅት በቀጥታ ከተሰጡት ሶስት ፕሮጀክቶች ውስጥ የማጠናቀቂያ ስራዎች የሚቀሩት የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የህንጻ ግንባታ ከላይ እንደተገለጸው ከተያዘለት የጊዜ በጀት በላይ ሶስት አመታት እንዲወስድ ይህ ሁኔታ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

38. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሀላፊዎች በዚህ ዙሪያ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ፕሮጀክቶቹ ለድርጅቱ ተሰጥተው የነበረው ድርጅቱ ከነበረበት እዳ እና ኪሳራ ውስጥ ለማውጣት ታስቦ እንደነበር ገልፀዋል፡፡

## የግንባታ እቃዎች አቅርቦትን በተመለከተ፣

39. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የግንባታ እቃዎች በተያዘላቸው የግዜ ሰሌዳ ውስጥ ሊቀርቡ ይገባል፡፡

40. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የግንባታ እቃዎች ፕሮጀክቶቹን ለሚገነቡ ስራ ተቋራጮች የሚቀርቡት የተያዘላቸውን የጊዜ ሠሌዳ ጠብቀው አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በግንባታ እቃዎች አቅርቦት መዘግየት ምክንያት ግንባታዎች በተደጋጋሚ ከወር በላይ እንደሚስተጓጎሉ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የግንባታ እቃዎች በወቅቱ አለመቅረብ ፕሮጀክቶች እንዲዘገዩ ምክንያት ከመሆኑ ተጨማሪ ስራ ተቋራጮች ላይ አላስፈላጊ ተጨማሪ ወጪ (overhead cost) እንደሚያስከትሉ ይታወቃል፡፡

41. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ እቃዎችን በራሱ ለማቅረብ የወሰነበት ዋና ምክንያት ወጪ እና ጊዜ ለመቆጠብ የነበረ ቢሆንም የግንባታ እቃዎች በጊዜ አለመቅረብ ጽ/ቤቱ ያስቀመጠውን አላማ እንዳያሳካ አድርጎታል፡፡

42. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የግንባታ እቃዎች ሲሚንቶ፣ አርማታ ብረት፣ ፕሪካስት ቢም እና ስላብ ብሎኬትን የሚያካትት ሲሆን ጽ/ቤቱ ሲሚንቶ እና አርማታ ብረትን ከገበያ ሲገዛ የተቀሩትን የኮንስትራክሽን እቃዎች ከተገጣጣሚ ሕንጻ አካላት ማምረቻ ድርጅት ያገኛል፡፡

43. ይህንን በተመለከተ የመ/ቤቱ ሀላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ለችግሩ ምክንያት የሆነው እንደ ከዚህ በፊቱ የአርማታ ብረት ለመግዛት የውጭ ምንዛሬ ባለመኖሩ እና የተገጣጣሚ አካላት ድርጅት ላይ በነበረ የአቅም ውሱንነት ምክንያት በተፈጠረ እጥረት ሳይሆን የግንባታ እቃዎች ስርጭት ላይ ባሉ መስተጓጎሎች እና ችግሮች እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

# ክፍል ሶስት

# መደምደሚያ

44. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጊዜ እና ገንዘብ ይቆጥባል ብሎ ያመነበትን ስታንዳርድ እና ወጪ ቆጣቢ ዲዛይን ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ቢሮዎች ህንፃ ግንባታ በማዘጋጀት እንዲያከናውን ኃላፊነት የተሰጠው ቢሆንም በፌዴራል መንግስት የሚደገፉ የመንግስት ቢሮዎች ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ እና የገንዘብ በጀት የማይጠናቀቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ይህ መሆኑ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተቀመጠለትን ተግባር በቁጠባ እና በብቃት እያከናወነ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ይህንንም ካደረጉት ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የጨረታ አሸናፊን ለማሳወቅ እና ኮንትራት ለመፈራረም መዘግየቱ፣ የግንባታ አቃዎቹን በወቅቱ አለማቅረቡ፣ ትክክለኛ ያልሆኑ ምክንያቶችን ተንተርሶ ለአንድ ስራ ተቋራጭ ሶስት ፕሮጀክቶችን በቀጥታ መስጠቱ ሲሆኑ፣ ይህም ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው የጊዜ እና የገንዘብ በጀት እንዳይጠናቀቁ ምክንያት ሆኗል፡፡ የግንባታዎች መዘግየት ፕሮጀክቶችን ለዋጋ መናር (inflation) የሚያጋልጣቸው ሲሆን፣ ይህም የግንባታ ፕሮጀክቶቹ ከተያዘላቸው የገንዘብ በጀት በላይ እንዲወጣባቸው ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቢሮ ህንፃዎች እንዲገነባላቸው የሚጠባበቁ የመንግስት መ/ቤቶች ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

- የመንግስት ቢሮዎች ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ እና የገንዘብ በጀት እንዲጠናቀቁ የሰራቸው ስራዎች እንዳሉ የኦዲት ቡድኑ ይገነዘባል፡፡ ሆኖም ግን በኦዲቱ ወቅት የታዩ ክፍተቶችን ለማጥበብ እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ግንባታዎችን ውጤታማ እና ብቃት ባለው መልኩ እንዲያከናውን የኦዲት ቡድኑ የሚቀጥሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርቧል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግንባታ እቃዎች ፍላጎት እቅድ በማውጣት እና የግንባታ እቃዎች የሚገኙበትን መንገድ ቀድሞ በመፈለግ እንዲሁም ለሚከሰቱ ችግሮች ከስራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች ጋር መደበኛ ግንኙነት በመፍጠር እና መፍትሄ በመስጠት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ እና የገንዘብ በጀት እንዲጠናቀቁ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጨረታ ካወጣ በኂላ በመንግስት የግዥ መመሪያ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የጨረታ አሸናፊዎችን በወቅቱ ሊያሳውቅ እና ኮንትራት ሊፈራረም ይገባል፡፡


- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚሰሩ የግንባታ ስራዎች ለማከናወን መወዳደር የሚችሉ ህንጻ ተቋራጮችን ሊያሳትፍ የሚችል ግልጽ የጨረታ ሂደት በማካሄድ እና በማወዳደር የተሻለ ብቃት ላላቸው ተወዳዳሪዎች ሊሰጡ ይገባል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግንባታ እቃዎችን አስቀድሞ በማከማቸት ለየፕሮጀክቶቹ አግባብ ባለው ጊዜ ሊያደርስበት የሚችል የስርጭት ዘዴ ሊቀይስ ይገባል፡፡

# አባሪዎች


**አባሪ 1**

## ድርጅታዊ መዋቅር




## የአሰራር ፍሰት ሥዕላዊ መግለጫ (process description)

### የቅድመ ግንባታ ማመቻቸት ስራዎች




አባሪ 2.1

## የኮንስትራክሽን ክትትልና ቁጥጥር ስራ ሥዕላዊ መግለጫ



አባሪ 2.2

## የዕቅድ አፈፃፀምና ግምገማ ስራ ፍሰት ሥዕላዊ መግለጫ



# የኦዲት ጥያቄዎች

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዓላማውን ለማሳካት እንዲችል የተዘጋጁ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች አሉትን?
- በዕቅድ የተያዙ አዳዲስ የግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ይጀመራሉን?
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚገነቡ ህንጻዎች በተቀመጠላቸው ወይም በተሻለ ንድፍ በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት ይጠናቀቃሉን?
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚወጡ ጨረታዎች የመንግስት የግዥ ሥርዓትን ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የግዥ ደንቦች ተከትሎ እንዲከናወኑ ይደረጋልን?
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ ክንውኑን ለመከታተል የሚያስችል ብቃት ያለው የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቷልን?

# የመመዘኛ መስፈርቶች

- የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ግንባታ  ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስራ የተቀላጠፈ እንዲሆን ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡
- የፌዴራል መንገስት ቢሮዎች ግንባታ ፕሮጀክቶች በተመደበላቸው በጀት እና ጊዜ መሰረት ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ  ስር ያሉ የጨረታ ሰነዶች ለህዝብ ተደራሽ ሊሆኑ ይገባል፡፡
- በመንግስት ህንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስር የሚፈፀሙ ግዢዎች በመንግስት የግዥ ሥርዓት መሠረት በግልጽ ጨረታ ሂደት ውስጥ ማለፍ አለባቸው፡፡
- የግንባታ ግብዓቶች ለያንዳንዱ ግንባታ በተያዘው የአቅርቦት እቅድ መሰረት እንዲቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የፌዴራል መንግስት ህንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በስሩ ባሉ ፕሮጀክቶች ላይ ዕለታዊ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚሰራው ስራ ሳምንታዊ ፣ወርሃዊ፣የመንፈቅ  እና አመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት፡፡

# ዋና ዋና የባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት

ከፕሮጅክት ጽ/ቤቱ በተጨማሪ በግንባታው ሂደት ሌሎች ዋናዋና ተዋናዩች አሉ፡፡

| ተ.ቁ | ባለድርሻ | የሚጠበቅባቸው ተግባር |
|---|---|---|
| 1 | አማካሪዎች | • ፕሮጅክት ጽ/ቤቱ በሚያወጣቸው የአማካሪ አገልግሎት ግዥ ጨረታ ላይ መሳተፍ<br>• የህንፃ ግንባታዎችን መቆጣጠር<br>• ለአሠሪው መ/ቤት ወርሃዊ የግንባታ ስራ ሪፖርት ማቅረብ |
| 2 | ህንፃ ተቋራጮች | • በፌዴራል መንግስት ቢሮ ህንጻ ግንባታ ጨረታ ላይ መሳተፍ<br>• በጨረታ የወሰዱዋቸውን ህንፃዎች ገንብቶ ማስረከብ |
| 3 | የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች | • ለቢሮ የሚጠቀሙበት ህንፃ እንዲገነባላቸው መጠየቅ<br>• ግንባታቸው የተጠናቀቁ ህንፃዎችን መረከብ |